ምሥጢረ ደብረ ታቦር!

mekrez.blogspot.com/2012/08/blog-post_8598.html

ገብረ እግዚአብሔር ኪደ

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፲፫ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.)፦ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፊሊጶስ ቂሳርያ ሰደቀመዛሙርቱ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል?" ብሎ ጠይቋቸው ነበር ፡፡ እነርሱም "እንዳንዶች ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ቅዱስ ነውና ኤርሚያስ ነው ይሉሀል ፤ እንዳንዶቹ ድንቅ የሆነ ልደትህንና የምታጠምቀውን አዲስ ጥምቀት አይተው መጥምቁ ዮሐንስ ነው ይሉሀል ፤ ሌሎች ደግሞ ሰአላቶችህ ቤት ያስህን ቅናት አይተው ኤልያስ ነው ይሉሃል" አሉት መልሰውለት ነበር ፡፡ ጌታችንም መልሶ ፦"እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው ፡፡ የሐዋርያት አፈጉባዔ የሚሆን ሲቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነህ" ብሎ መልሷል ፡፡ ጌታም "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም (ምድራዊ መምህር) ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ" ብሎታል ፡፡

ከዚህ በኋላ ጌታችን በኢየሩሳሌም ካህናት ሊቀካህናት ጸሐፍት ፈሪሳውያን ስለሚያደርሱበት መከራ ስለሚሞተው ሞት ይነግራቸው ጀመር ፡፡ ሰይጣንም አስቀድሞ በቀዳማይቱ ሔዋን እንዳደረገው አሁንም በስምዖን ጴጥሮስ እንደበት ወዳጅ መስሎ "አይሆንም አይደረግም" በማለት መከራከር ጀመር ፡፡ ጌታችን ግን ጴጥሮስን አድርጎ ሰይጣንን ይገስጸው ጀመር ፦"ጴጥሮስ ሆይ! የእኔ አመመጣጥ ሰምን እንደሆነ አታስተውልምን? የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! በቤተልሔም ተወልጄ ከሴቶች ሰሚወለዱ ሕፃናት ሁሉ ደስታ እንደሆንኩላቸው አሁንም የእኔን እዚያ መውረድ እየተጠባበቁ የሚገኙትን ቅዱሳን ወደገነት አመልስ ዘንድ ሲያልመሄድ አለብኝ ፡፡ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን ይህን ሲያዩ ይመኛሉና ፤ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ይናፍቃልና ፡፡ ስለዚህ እያቸው ዘንድ መውረድ አለብኝ ፤ እጎበኛቸው ዘንድ ልሞት ልሰቀል ይገባኛል ፡፡ በእውነት ሰይጣን ካልሆነ በቀር የእኔን መሰቀል የሚቃወም የነፍሳትም ነፃመውጣት የማይናፍቅ ማን ነው? እንተ ጴጥሮስ! ይህን ሁሉ የምትሰኝ ሰይጣን በእንተ ተመለሱ እንድም እንተውራስህ ለእኔ ካለህ ፍቅር የተነሣመሆኑን ብረዳም ጀርህ ትንቢተ ነቢያትን ባይሰማይልቁንም ዓሣማጥመድን ብቻ ለሰሚያውቅ ነውና ወግድ" አለው ፡፡

ይህም በሆነ በሰባተኛው ቀን ሦስቱን ደቀ መዛሙርት ማለትም ጴጥሮስ ፣ ዮሐንስንና ያዕቆብን ይዞ ወደታቦር ተራራ ወጣ ፡፡ክርስቶስ ባይሞት እንዴት ያለ ከብር እንደሚቀርባቸው ያሳያቸው ዘንድ ምስክርም እንዲሆኑ እነዚህን ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ይዞ ወጣ ፡፡በዚያም እንደዮርዳኖስ ወንዝ መድኃኔዓለም ከብረ መንግሥቱን ፣ ብርሃነ መለኮቱን ገልጠሳቸው ፡፡በየዓመቱ ነሐሴ 13 ቀን ቤተ ክርስቲያናችን ከምታከብራቸው ዘጠኙ ዐበይት የጌታ በዓላት አንዱ የሆነው በዓለ ደብረታቦር የዚህ ታሪክ መታሰቢያ ነው ፡፡በዚህ ዕለት ሕፃናት ጅራፋቸውን ገምደው እያስጮኹ ይጨፍራሉ ፡፡ይኸውም ጅራፍ ሲጮህ እንደሚያስደነግጥ ሁሉ ከጌታ ጋር የነበሩት ሦስቱ ደቀ መዛሙርትም አብ በደመና ሆኖ ሲናገር መደንገጣቸውንና መውደቃቸውን የሚያስታውስ ነው ፡፡

ታቦር ተራራ ከገሊላ ባሕር በምዕራራባዊ ደቡብ በኩል 10 ኪሎ ሜትር ርቀት

ሳይ ፣ ከናዝሬት ከተማ በስተምሥራቅ ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ተራራ ነው ።ተራራው ከባሕር ወለል በሳይ 572 ከፍታ አለው ።ብዙ ሰዎች ከሳይ ወደታች ሲታይ ታቦር ተራራ ቅርጹ የተገለበጠ የሻይ ስኒ ይመስላል ይሳሉ ።



ምሥጢረ መንግሥቱን ለምን በታቦር ተራራ ገለጸው?

መድኃኔዓለም ሌሎች ተራሮች እያሉ ክብሩን ለመግለጥ ለሰማን ደብረ ታቦርን መረጠ ቢሉ ትንቢቱንና ምሳሌውን ለመፈጸም ነው ።

1. ***ትንቢቱን ለመፈጸም***

“ታቦርና አርሞንኤም በስምህ አምነው በተደረገላቸው ነገር ደስ ይላቸዋል ፣ ስምህን ያመሰግናሉ ፣ ለስምህም ምስጋና ያቀርባሉ” እንዲል /መዝ. 88 ፡12/ ።

2. ***ምሳሌውን ለመፈጸም***



ይህ ተራራ ባርቅ ሲሳራን ድል አድርጎበታል /መሳ .4 ፡6/ ።ታሪኩም እንዲህ ነው ።

“የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደገና ክፉ ሥራ ሠሩ ።እግዚአብሔርም በአሶር በነገሠው በከነዓን ንጉሥ በኢያቡስ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው ፤ የሠራዊቱም አለቃ በአሕዛብ አሬሶት የተመረጠው ሲሣራ ነበር ፡፡... ዘጠኝ መቶ የብረት ሰረገሎች ነበሩትና የእስራኤልን ልጆች ሃያ ዓመት ያስጨንቃቸው ነበር” /መሳ 4.1-3/ ።ሁሌም ቢሆን የሰውን በደል በይቶ እንደወጣችሁ ግቡት ፣ እንደገባችኋት ውጧት የማይልና “ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል” የተባለለት እግዚአብሔር ከዚህ ቀን በር የሚላቀቁበትን መላ ራሱ አመለከታቸው /1ቆሮ. 10-13/ ።እስራኤላውያን ወደ ፈጣሪያቸው በጮኹ ጊዜ የሰፈሮት ሚስት የሆነችውንና እስራኤልን በነቢያነትና ዳኝነትታገለግል የነበረችው ነቢይቱን ዲቦራን ተጠቅሞ የማሸነፊያ መላውን አመለከታቸው ።ነቢይቱ ዲቦራ ትንቢት ከመናገር አልፋ የእስራኤልን ንጉሥ ባርቅ ከእኔ ጋር ወደ ጦርነቱ ውጪ ብሎ ባስጨነቃት ጊዜ በጦር አዝማችነትም ተሳተፈች ።እግዚአብሔር በነቢይቱ በዲቦራ በኩል ለእስራኤል ንጉሥ “ሒደህ ወደ ታቦር ተራራ ውጡ” ብሎ አዞት ነበርና ንጉሡ ዐሥር ሺሕ ብረት ለበስ ያልሆነ እግረኛ ሠራዊት ይዞ ደብረ ታቦርን ተማምኖ በተራራው ሳይ መሸገ ፤ ጦርነቱም ሳይጀመር አለቀ ።ምክንያቱም “እግዚአብሔርም ሲሣራን ሰረገሎቹንም ሁሉ ሠራዊቱንም ሁሉ ከባርቅ ፊት

በሰይፍ ስለት አስደነገጣቸው ።ሲሣራም ከሰረገላው ወርዶ በእግሩ ሸሸ"/መሳ. 4.15/ ።እስራኤል በእግዚአብሔር አጋዥነት በታቦር ተራራ ሳይ የሃያ ዓመት የግፍና የሰቀቀን አገዛዝ ቀንበራቸውን ከትከሻቸው አሽቀንጥረው በምትኩ የድል ካባን ደረቡ ።"በቦርነት ኃይለኞች ሆኑ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ" ተብሎም ጀግንነታቸው ተጻፈላቸው ።የታቦር ተራራ ያኔ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባለውለታቸው ነበር /ዕብ. 11.32-34/ ።ጌታም በልበ ሐዋርያት ያለ ሰይጣንን ድል ያደርግበታልና ማለትም በልባቸው ጥርጥርን እና ፍቅረ ሢመትን (የሥልጣን ፍቅር) ያሳደረ ዲያብሎስን ድል ነስቶላቸዋል ።ከዚህም በመነሣት ነው "በዓለ ደብረታቦር የደቀመዛሙርትተማሪዎች በዓል ነው" የሚባለው ።

ለምን ሦስቱን ሐዋርያት ብቻ ይዞ ወጣ?

1. ጌታ "እሞታለሁ፤ እሰቀላለሁ" ባለው ጊዜ ጴጥሮስ "ልትሞት አይገባም፤ ይህ ላንተ አይገባም" ብሎ ተቃውሞት ነበርና በአብ ቃል "እርሱ ያላችሁን ስሙት፤ ይህ ለእንተ አይገባም አትበሉት፤ አትቃወሙት" ሰማስት ።
2. ጌታ "እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?" ብሎ ደቀመዛሙርቱን በጠየቃቸው ጊዜ ጴጥሮስ "አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ብሎት ነበርና አሁንም አብ "አዎ ልክ ነህ! እመለከበት ዘንድ ለተዋሕዶ የመረጥኩት የምወደው ልጄ ይህ ነው" ብሎ ሰማረጋገጥ ።
3. ለፍቅሩ ለሰሚላቸው ነው ።ይህም በዕብራይስጡ ኬፋ ፤ በግሪኩ ጴጥሮስ ፤ በግዕዙ ኩኩሕ (ዐለት) የተባለው የዮና ልጅ ስምዖን ጌታችን "እሞታለሁ" እያለ ሲናገር "አይሁንብህ" ማለቱ አለቀድመን እንደተናገርን "ለጌታ ካለው ፍጹም ፍቅር የተነሣ ነው" ይላል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ።ዮሐንስም በወንጌል "የጌታ ወዳጅ" ተብሎ ተጽፏል ።ያዕቆብ ደግሞ ጌታን በእጅጉ እንደሚወደው በኋላ ታውቋል ።ይኸውም "እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ?" /ማቴ.20 ፡20/ሲባሉ "አዎ" ብሎ መመለሱና በዚህም በሄርድስ ዘአግሪጳ ሰማዕትሆኖ መሞቱ ምስክር ነው ።
4. በይሁዳ ምክንያት ነው ።"ንጥእ ሰው የእግዚአብሔርን ክብር እንዳያይ ያርቁታል" እንዲል /ኢሳ 26:13/ እርሱን ጥሎ አሥራ አንዱን ወደ ተራራ ይዞ ቢወጣ ከምሥጢር ቢሰየኝ በሞቱ ገባሁበት እንዳይል ።ያም ባይሆን ስምንቱ ደቀመዛሙርት ሰምን ይከሰክሳሉ ቢሉ አልተከሰከሱም በርዕሰ ደብር (በተራራው አናት) ሰሠስቱ ደቀመዛሙርት የተገለጸው ምስጢር በእግረ ደብር (በተራራው ግርጌ) ሰነበሩት ስምንቱ ደቀመዛሙርት ተገልጦላቸዋል ።ይህም በደብረሲና ሰሰባው ሲቃናት የተገለጠ ምሥጢር በከተማ ሰነበሩት ሰኤልዳድና ሙዳድ እንደተገለጠ ማለት ነው /ዘኁ.11 ፡26/ ።

ኤልያስና ሙሴን ለምን አመጣቸው?

1. በእንድ ወቅትሙሴ እግዚአብሔርን ፦"በእንተ ዘንድ ባለሟልነትን ማግኘቴ እውነት ከሆነ ስፊት ለፊትተገልጸህልኝ ልይህና በእንተ ዘንድ ባለሟልነትን ማግኘቴን ልወቀው" ሲል ጠይቆት ነበር ።እግዚአብሔርም "ጀርባዬን ታያለህ ፊቴን ግን አታይም" ብሎት ነበር /ዘጸ. 33.13 ፣ 23/ ።የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜና ሐተታ በደብረ ታቦር ተፈጽሟል ።እንዲህ ማለቱ "እምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ሰውሆኜ ሥጋ ለብሼ ኋላ በደብረ ታቦር እስከገለጽልህ ድረስ እንተ በመቃብር ተወስነህ ትኖራለህ" ማለቱ ነበርና ።ይህን ማለቱ እንደሆነ የታወቀው ግን በደብረ ታቦር ሙሴን ከብሔረ ሙታን በአካለ ነፍስ አምጥቶ ባቆመው ጊዜ ነበር ።
2. ልዑል እግዚአብሔር ነቢዩ ኤልያስን ፦"እንተ በኋለኛው ዘመን ምስክር ትሆነኛለህ" ብሎት ነበር ።ይኸውም ኃይለ ቃል ኤልያስ ከብሔረ ሕያዋን መጥቶ

“የእኔን የኤልያስን ጌታ ማን ኤልያስ ነው ይልሃል? እግዚአ ኤልያስ፤ አምላከ ኤልያስ ይበሉህ እንጂ” ሲል በደብረ ታቦር ተፈጸመ። ታያለህ የተባለውሙሴም አየ፣ ትመሰክራለህ የተባለውኤልያስም መሰከረ።
3. በፊልጶስ ቂሳርያ ጌታ ሐዋርያትን “ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል?” ብሎ በጠየቃቸው ጥያቄ ሲመልሱ “ሙሴ ነው ይሉሃል፤ እንዲሁም የኃይል ሥራህን ተመልክተው ኤልያስ ነው ይሉሃል” ብለውነበርና ሙሴን ከመቃብር፤ ኤልያስን ከብሔረ ሕያዋን አምጥቶ እግዚአ ሙሴ፤ አምላከ ሙሴ፤ እግዚአ ኤልያስ፤ አምላከ ኤልያስ መሆኑን ሰማስመስከር።
4. አይሁድ ፈሪሳውያን ጌታን እንደ ሕግ ተላላፊና የእግዚአብሔርን ክብር ሰራሱ የሚወስድ አድርገው ያስቡት ስለነበረ /ዮሐ.9፡16፣ 10፡33/ ሕግን የሰጣቸው ሙሴንና ለሕገ እግዚአብሔር ቀናተኛ የነበረውኤልያስን አምጥቶ ሕግ አፍራሽ አለመሆኑን የእግዚአብሔር ተቃዋሚም አለመሆኑን ሰማስረገጥ።
5. ጌታችን በሙታንና በሕያዋን ላይ ሥልጣን ያለው እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ ሞተው ከተቀበሩትሙሴን ከብሔረ ሕያዋንም አልያስን አምጥቶ ሲነጋገር ታየ።
6. የሐዋርያቱን የወደፊት አገልግሎት ሲነግራቸው። ይኸውም ሙሴ እና ኤልያስ ለሕዝበ እስራኤል በጣም ታማኝ እንደነበሩ ሁሉ እነርሱም ለሚያገለግሉት ሕዝብ ታማኝ እረኞች እንዲሆኑ። ሆኖም ግን አገልግሎታቸው ከሙሴና ከኤልያስ ይልቅ ጠንከር እንደሚልም አሳይቶአቸዋል። ምክንያቱም ውጊያቸው እንደሙሴ ከፎርዖን እንደኤልያስም ከአክዓብ ጋር ሳይሆን ከክፋት መናፍስት ጋር ነውና።
7. ጽድቃቸው ከእነዚህ ከሙሴና ከኤልያስ የበለጠ ሊሆን እንደሚገባ ሰማሳየት /ማቴ.5፡20/። ምክንያቱም ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ቢመራ ምድረ ፍልሥጤምን ሰማውረስ ነው። እነዚህ ግን ሕዝቡን መርተው የሚያስገቡት መንግሥተ ሰማያትን ነው። ኤልያስ ሰማያትን ቢሰጉምም ከጊዜአዊ ዝናም ነው። እነዚህ ግን ለዘለዓለም መንግሥተ ሰማያትንም የመሰጎም ሥልጣን አላቸውና።

ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ “ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው” ሲል ተደምጧል። ይህም የተሰየየ ትርጉም አለው። ቃል በቃል (Literaly) ስናየው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታ ሆይ በዚህ መኖር ለእኛ መልካም ነው ማለቱ “እንተ እያበሳኸን እየፈወስከን፣ ሙሴ እነዚህ መከራ ያደርሱቡኖል ይገድሉኖል ያልካቸውን ጸሐፍትና ፈሪሳውያን እንዳይመጡ በደመና እየጋረደ፣ ቢመጡም አልያስ እሳት እያዘነመ እያባረራቸው በዚህ መኖር ለእኛ መልካም ነው” ማለቱ ሲሆን ምሥጢራዊው መልእክቱ ግን “የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በሚታመን በት፣ ወልድ ዋሕድ በምትሰው ሃይማኖት መኖር ለእኛ መልካም ነው። ሰይጣን ድል በተደረገባት በታቦር ተራራ ምሳሌም በምትሆን በወንጌል ሕይወት፣ እንድም በቤተ ክርስቲያን መኖር ለእኛ መልካም ነው” ማለቱ ነው።

ታቦር ተራራ የወንጌል ምሳሌ ነው!

ተራራ ሲወጡት ያደክማል፣ ከወጡት በኋላ ግን ጭንጫውን፣ ግጫውን ሲያሳይ ደስ ያሰኛል። ወንጌልም ሲማሯት ትከብዳለች በኋላ ግን ጽድቅን እና ኃጢአትን ሰይታ ስታሳውቅ ደስ ታሰኛለች።

ታቦር ተራራ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነው!

ሀ. በታቦር ተራራ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ኤልያስና ሙሴን ፣ ከሐዲስ ኪዳን ሦስቱን ሐዋርያት እንደተገኙ በቤተክርስቲያን ብሉይ ከሐዲስ እንዲነገር ያጠይቃል ። ሐዋርያት የሰበኩት ወንጌል አስቀድመው ነቢያት በምሳሌና በትንቢት የተናገሩት እንደሆነ ያስረዳል ።“ነቢያት በቀየሱ ሐዋርያት ገሰገሱ” እንዲል ጳውሎስም “በሐዋርያት በነቢያት መሠረት ሳይ ታንጻችኋል” ይላልና /ኤፌ 2 ፣ 20/ ።
ሰ. በታቦር ተራራ ከመዓስባን (ባሰትዳር)ሙሴን ከደናግል ደግሞ ኤልያስ እንደተገኙ በቤተክርስቲያን በድንግልና የሚኖሩ መናንያን መነኮሳት ፣ በሕግ በሥርዓት የሚኖሩ ባሰትዳርኞም ይገኛሉና ።

ታቦር ተራራ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው!

1. ተራራ በብዙ ጭገር እንዲወጡት ወደ እግዚአብሔር መንግሥትም በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናልና /ሐዋ 14 ፡22/ ።
2. በታቦር ተራራ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከሐዲስ ኪዳንም ሐዋርያት እንደተገኙ መንግሥተ ሰማያትን ነቢያትም ፣ ሐዋርያትም እንድሆነው ይወርሷታልና ።
3. በታቦር ተራራ ከመዓስባን ሙሴ ከደናግል ደግሞ ኤልያስ እንደተገኙ መንግሥተ ሰማያትንም ደናግልም መዓስባንም በእንድ ሳይ ይወርሷታልና ።
4. በታቦር ተራራ ሞተው ከተቀበሩት መካከል ሙሴን በብሔረ ሕያዋን ካሉት ደግሞ ኤልያስን እንደመጡ መንግሥተ ሰማያትንም ሞተው የተቀበሩትም በብሔረ ሕያዋን ያሉትም በእንድነት ይወርሷታልና ።

በአጠቃላይ ታቦር ተራራ የክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት የተመሠከረበት ፣ የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት የተሰጠበት ፤ ፈጣሪ ከቅዱሳን ሰዎቹ ጋር የተገኘበት ፤ በልበ ሐዋርያት የነበረ ሰይጣን ድል የተደረገበት ፤ የሐዋርያት በተሰይም የሥልጣናት የተገለጠበት ፤ አሉባልታና ተራ ወሬ የከሸፈበት ፤ የቅዱሳንን ክብር ለሚያናንቁ ተራራም እንኳን “ቅዱስ” እንደሚባል የተማርንበት ፤ የብሔረ ሕያዋን መኖር የተመሰከበረበት ፤ የትንሣኤ ሙታን ዋስትና የተገለጠበት የክብር ሰገነት ፣ የምሥጢር መቅደስ ፣ ታላቅ ትምህርት ቤትም ጭምር ነው ።
ፈጣሪ ያጭን እግዚአብሔር እስከ መጨረሻዋ ሕቅታ ድረስ በታቦር ተራራ በተመሰለጭ ቤተክርስቲያን በሃይማኖታጭን ጸንተን የመንግሥተ ሰማያት ወራሾጭ የስሙ ቀዳሾጭ እንድንሆን የእግዚአብሔር ጥርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን ።አሜን !!